# ነገረ ክርስቶስ

## በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ


<u>አዘጋጅ</u>

አቤል ሚካኤል




መጋቢት 2002 **ዓ.ም**



www.eotc-mkidusan.org

በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡» 1ኛ ቆሮ.
15÷20-21



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷአል፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡» 1ኛ ቆሮ. 15÷20-21



**«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና፡፡» ሉቃ.** 1፥49

# 1. መግቢያ

ብርህት፣ ንጽህት፣ ጽድልት፣ የሆነች ቤተክርስቲያናችን ከምታስተምራቸው ትምህርቶች አንዱና ዋነኛው ነገረ ክርስቶስ /Christology/ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን ትምህርት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ሥላሴ አንዱ አካል ወልድ ሲሆን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ በኋላኛሲሆን ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ሰው ሆነ፡፡

ጌታችን ሁለት ልደቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአባት ብቻ የተወለደው ሲሆን፤ ሁለተኛው ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከእመቤታችን የተወልደው ነው፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ንጉሥ ዳዊት ስለቀዳማዊ ልደቱ ሲናገር «አንተ ልጄ ነህ፡፡ እኔ ዛሬ ወለድሁህ» ብሎአል /መዝ.2፥7/ ቅዱስ ጳዉሎስም ስለ ደኅራዊ ልደቱ ሲናገር «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግ በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» /ገላ.4፥4/ ብሎአል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ ቤተክርስተያን ጌታችን ሁለት ልደታት እንዳሉት ትመሰክራለች፡፡ ቅዱስ ሳዊሮስም ቀዳማዊ ልደቱ በድኃራዊ ልደቱ እንደታወቀ በሃማኖት አበው አስተምሯል፡፡

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኋላኛው ዘመን ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ቢሆንም ከአምላክነቱ ክብር አልጎደለበትም፡፡ ይህም ማለት ጌታችን ሰው ሲሆን አምላክ፤ አምላክ ሲሆን ደግሞ ሰው ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳዉሎስም ይህን ሲገልጽ «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም» ብሏል፡፡ /ፊሊ.2፥6/ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በቅዳሴው «ከአንድነቱ ሳይለይ መጣ፡፡ ከሦስትነቱ ሳይለይ ወረደ፡፡ ከሙላቱ ሳይጐል በማሕጸን ተወሰነ.....» በማለት የጌታችንን አምላክ ሲሆን ሰው መሆን አስተምሯል፡፡ ወንጌልም ጌታ በምድር ሲመላለስ ከአባቱ እንዳልተለየ ትገልጻለች፤ «በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው» ዮሐ.1፥18 ፡፡

ቤተክርስቲያናችን ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በቂሣርያ የመሰከረውን፣ ሐዋርያት የሰበኩትንና ሊቃውንቶቿ ያስተማሩትን መሠረት በማድረግ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ፣ ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር፣ መድኃኒት ወዘተ እንደሆነ ታምናለች ታስተምርማለች፡፡ ቤተክርስቲያናችን ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት አምልታና አስፍታ የምታስተምር ሲሆን እኛ ግን በጥቂቱ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

### ሀ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒት /አዳኝ/ ነው

ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያናችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ልጆች ሁሉ ከኃጢአያት ደዌ ያዳናቸው መድኃኒት እንደሆነ ታስተምራለች፡፡ ለዮሴፍ በህልሙ የታየው የእግዚአብሔር መልአክ «ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ኢየሱስ ትለዋለህ» ሲል ተናግሯል፡፡ ማቴ.1፥21 ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬምም ይህን ቃል በመያዝ «.. ዘያድህኖሙ ለሕዝቡ እምኃጢአቶሙ.. ሕዝቡን ከኃጢአታቸው የሚያድናቸው ነው» በማለት ተናግሯል፡፡ ውዳሴ ማርያም ዘሐሙስ፤ ለኖሎት /ለእረኞች/ የጌታችንን መወለድ ያበሰራቸው መልአክ «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል» በማለት የክርስቶስን መድኃኒትነት ነግሯቸዋል፡፡ /ሉቃ.2፥11/ ሐዋርያትም የጌታቸውን መድኃኒትነት ሲመሰክሩ «መዳን በሌላ በማንም የለም፡፡ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» በማለት የክርስቶስን ብቸኛ መድኃኒትነት ይገልጻሉ /ሐዋ.4፥12/፡፡ ሳምራዊቷ ሴት ስለ ክርስቶስ የነገረቻቸው የሰፈሯ ሰዎች «እርሱ በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን» ብለዋል /ዮሐ.4፥42/፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚከተሉትን ጥቅሶችም ይህንኑ ያስረዳሉ /ሐዋ.5 ፥ 31፤ ሐዋ.13፥32፣ ሮሜ.11፥26፣ ፊሊ.3 ፥20፣ 2ጴጥ.3፥2/፡፡

### ለ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ነቢያት፣ ሐዋርያትና ጌታችን ራሱም በስፋት የመሰከሩ ሲሆን ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመልከት

- ኢሳ. 9፥6 «ሕፃን ተወልዶልናልና.. ስሙም ድንቅ፣ መካር፣ ኃያል፣ አምላክ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡»
- ዮሐ. 10፥30 «እኔና አብ አንድ ነን»
- ሮሜ.9፥5 «ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፡፡ አሜን»
- ቲቶ.2፥13 «..እርሱም የታላቁ አምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን..»
- 2ጴጥ.1፥1 «በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ..»
- 1ዮሐ. 5፥20 «እርሱም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው፡፡»

- *ራዕይ* 1፥7 «.. *ፊተኛውና መጨረሻው ህያውም እኔ ነኝ*..»

*እነዚህንና ሌሎችን መሠረት በማድረግ ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ ታምናለች ፤ ትመሰክራለች።*

**ሐ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው**

*ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርነት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የመሰከሩ ሲሆን አባቶቻችንም አምልተውና አስፍተው አስተምረዋል። ቅዱስ ዮሐንስ ምስጢረ ሥጋዌን በተናገረበት አንቀጽ «ቃልም እግዚአብሔር ነበር.. ቃልም ሥጋ ሆነ» ብሎአል። /ዮሐ.*1፥14/ *ዳግመኛም ንጉሥ ዳዊት ስለ ክርስቶስ ዕርገት በዘመረበት መዝሙሩ «ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን.. እግዚአብሔር በመለከት ድምጽ ዐረገ።» ብሎአል /መዝ.*46፥5/። *ቅዱስ ሉቃስም ግብረ ሐዋርያትን ሲጽፍ «.. በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ...» በማለት ደሙን በቀራንዮ ያፈሰሰው ኢየሱስ ክርስቶሰ እግዚአብሔር እንደሆነ መስክሯል። ቅዱስ ቄርሎስም* <u>*«እስመ እግዚአብሔር ውእቱ ወአኮ ገብር ወተለዐለ ኀበ ስብሐተ እግዚአብሔር ወዳዕሙ ነሥአ አርአያ ገብር እንዘ ሀሎ በ፩ዱ ዕሪና ምስለ አብ ወኢኮነ ሰብአ ወእምዝ ረከበ ብዕለ መለኮት»*</u> ... *«እርሱ እግዚአብሔር ነውና ተገኘ ሆኖ ኖሮ ወደ እግዚአብሔርነት ክብር የደረሰ አይደለም፤ ከአብ ጋር በአንድ ትክክልነት ሳለ የተገኘ ባሕርይን ነሣ እንጂ መለኮት ሰው ሆኖ ኋላ ክብርን ያገኘ አይደለም» ብሎአል። ስለዚህ ሐዋርያት እንዳስተማሩት ሊቃውንትም እንደመሰከሩት፣ ቤተክርስቲያናችንም እንደምታምነው ኢየሱሰ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው።*

**መ. ጌታችን ኢየሱሰ ክርስቶስ ፈጣሪ ነው።**

*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉ ነገር አስገኝና ፈጣሪ ነው ቅዱስ ዮሐንስም በወንጌሉ «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳችስ እንኳ ያለ አርሱ አልሆነም» በማለት ፈጣሪነቱን መስክሯል /ዮሐ.*1፥3/። *ዳግመኛም ቅዱስ ጳውሎስ «ሁሉ ለእርሱና በእርሱ ተፈጥሯል» ብሎአል /ቆላ.*1፥16/። *ቅዱስ ኤፍሬምም በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ «እስመ ውእቱ ፈጠረነ.. እርሱ ፈጥሮናልና» በማለት የጌታን ፈጣሪነት መስክሯል። /ውዳሴ ማርያም ዘአርብ/።*

**ማጠቃለያ**

«... **ጌታችን አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል**...» / **ራእይ** 4፥10/

## 2. ነገረ ተዋሕዶ

ተዋሕዶ የሚለው ቃል የሁለት ነገሮችን አንድ መሆን ያመለክታል፡፡ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው በተዋሕዶ ነው፡፡ የተዋሕዶን ነገር ለመመልከት በመጀመሪያ የጌታችንን ሰው የመሆንን አስፈላጊነት እንመልከት፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ መልካም የሆነች ረዳትም ከጎኑ ፈጠረለት፤ በሌሎቹ ፍጥረታትም ላይ ገዢ አድርጎ ሾመው፤ ከገነት ዛፎች ሁሉ ከአንዷ በቀር ይበላ ዘንድ ፈቀደለት፡፡ ነገር ግን አዳም ፍጡርነቱ ይታወቅ ዘንድ ይልቁንም ደግሞ ነፃ ፈቃዱ ይገለጥ ዘንድ መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ /እጸ በለስ/ እንዳይበላ ከለከለው፡፡ አዳምም ይህንን ሕግ መሠረት በማድረግ በገነት ውስጥ ለጥቂት ዓመታት በሰላምና በደስታ ኖረ፡፡ ነገር ግን አዳም በሰይጣን ተንኮል ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሶ እጸ በለስን በላ፡፡ በዚያ ቅጽበት አዳም ጸጋው ተገፈፈ፤ ባሕርይው ጎሰቆለ፡፡ አዳም ገነትን የመሰለች ቦታ እግዚአብሔርን የመሰለ ጌታ አጣ፡፡ ሞትን የሚያህል እዳ ተሸክሞ ከገነት ተባረረ፡፡ ነገር ግን ፍጥረታትን የማይረሳ እግዚአብሔር አዳምን እንደሚያድነው ቃል ገባለት፡፡ ለመሆኑ ለአዳም መዳን የሚያስፈልገው ማነው?

መላእክት ከእግዚአብሔር እየተላኩ ሰውን ይራዱ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሰውን ጸሎት ወደ እግዚብሔር ያደርሱ ያደርሳሉ ያማልዱም ነበር፡፡ ነገር ግን የአዳምን እዳ ማስወገድ አልቻሉም መዝ. 33፥7፤ ዘካ. 1፥12፤ መሣ. 6፥20፤ ዳን. 7፥16፤ ዳን. 10፥13

ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ፤ የሕዝቡንም መልእክት ወደ እግዚአብሔር ያደርሱ ነበር ከዚህም ውጪ አንገታቸውን ለሰይፍ ጀርባቸውን ለጅራፍ ሰጥተው ሰማዕት ሆነዋል፡፡ ከአቤል ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ድረስ የነቢያት ደም እንደ ጎርፍ ፈሷል፡፡ ሆኖም ግን ነቢያትም ቢሆኑ የአዳምን እዳ ለመክፈል አልቻሉም፡፡ ኢሣ. 1፥1፤ ሕዝ. 1፥1፣ ኢሳ. 64፥1

በሕገ ኦሪት ይሰዉ የነበሩት በጎች፣ ፍየሎች፣ ዋኖሶችና ርግቦች ወዘተ መስዋዕቶች ለጊዜው የሰውን ኃጢያት ያስተሰርዩ እንጂ የአዳምን እዳ ለመክፈል አልቻሉም ነበር፡፡

በአዳም የፈረደበት እግዚአብሔር ነው እንደሚያድነውም ቃል የገባለት እግዚአብሔር ነው። ከዚህም ውጪ አዳም የነበረበትን እዳ የመክፈል አቅም /ሥልጣን/ ያለው ብቸኛ አካል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ነገር ግን የአዳምን እዳ መክፈል ያለበት አዳም ነው። ቢሆንም ግን አዳም እዳውን ለመክፈል ከአቅሙ በላይ ነበር። ስለዚህ አዳም እንዲድን የግድ እግዚአብሔር ሰው መሆን ነበረበት። በዚህም መሠረት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ሥጋ ተዋሕዶ ሰው ሆነ።

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ተዋሕዶ ስንል ሥጋዊ አካል ከመለኮታዊ አካል፣ መለኮታዊ አካል ከሥጋዊ አካል ሥጋዌ ባሕርይ ከመለኮታዊ ባሕርይ መለኮታዊ ባሕርይ ከሥጋዊ ባሕርይ አንድ ሆነ ማለታችን ነው።

ይህም ማለት ጌታችን ከሁለት አካል /ከሥጋዊ አካልና ከመለኮታዊ አካል/ አንድ አካል፣ ከሁለት ባህርይ /ከሥጋዊ ባህርይና ከመለኮታዊ ባህርይ/ አንድ ባህርይ ሆኗል ማለት ነው። ይህ ተዋሕዶ በተአቅቦ /በመጠባበቅ/ ማለትም ሁለቱ ባህርያ ሳይጠፉ ነው። ቤተ ክርስቲያናችንም የአካልንም የባህርይንም ተዋሕዶ እንደሚከተለው ታስተምርማለች።

## *2.1 የአካል ተዋሕዶ*

የቤተ ክርስያናችን መሠረተ እምነት ከሆኑት ትምህርቶች መካከል አንደኛው የሥጋዊ አካልና የመለኮታዊ አካል ተዋሕዶ ነው። በምስጢረ ሥላሴ ትምህርት ሥላሴ በአካል ሦስት እንደሆኑ እንማራለን። ለእያንዳንዳቸውም ፍፁም መልክዕ፣ ፍጹም ገፅ፣ ፍጹም አካል እንዳላቸው እናውቃለን። መለኮታዊ አካል ግን የማይታይ የማይዳሰስ የማይጨበጥ ረቂቅ ነው። በሌላ በኩል ሥጋዊ አካል ግዙፍ የሚታይ የሚዳሰስ እንደሆነ እናውቃለን። በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የእነዚህ የሁለት አካላት /የሥጋዊ አካልና መለኮታዊ አካል ተዋሕዶ/ የአካል ተዋሕዶ ይባላል። ይህንንም መጻሕፍት በምልዐትና በስፋት ይመሰክራሉ። ጌታችን ከአይሁድ ጋር በተከራከረበት ምዕራፍ «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው» ዮሐ. 8÷58። በዚህ ዐረፍተ ነገር አብርሃም ሳይወለድ ጌታ እንደነበር ቢናገርም ጌታችን በሥጋዊ አካል ከተገለጠ ገና ሃምሳ ዓመት እንዳልሞላው አይሁድ ተናግረዋል። ነገር ግን ሥጋዊ አካል ከመለኮታዊ አካል ጋር በመዋሀዱ የመለኮትን ገንዘብ፣ ገንዘብ ያደረገው የሥጋ አካል ከአብርሃም በፊት ነበርኩ አለ። ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶሰ ክርስቲያኖች «አውቀውስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር።» ብሎአቸዋል። 1ቆሮ. 2÷8 ይህም በቀራንዮ ደሙን

ያፈሰሰው የክብር ጌታ እግዚአብሔር ከሥጋ ጋር ፍፁም መዋሐዱን ያመለክታል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም በመቅደስ አይሁድን በገሰፀበት ስብከቱ «የሕይወትን ራስ ገደላችሁት» ብሎአቸዋል፡፡ ሐዋ. 3፥14-15፡፡ ይህም አይሁድ በክፋት የገደሉት የሕይወት ራስ ክርስቶስ ሥጋን የተዋሐደ መለኮት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ ጌታችን ከተገለጠለት በኋላ «ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ» ብሎታል፡፡ ራዕ. 1፥17 ፊተኛው መጨረሻው ብሎ መለኮቱን ሲገልጽ ሞቼም ነበርሁ ብሎ ከሥጋ ጋር ፍጹም መዋህዱን ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ጌታችን በተዋሕዶ ከሁለት አካል አንድ አካል ነው ብለን እናስተምራለን፡፡

### *2.2 የባሕርይ ተዋሕዶ*

መለኮትና ሥጋ ሁለት የተለያዩ አካላትና ባህርያት አላቸው፡፡ መለኮታዊ ባሕርይ የምንለው በሁሉ ቦታ መገኘት፣ ሁሉን ማድረግ መቻል ዘለዓለማዊነት እና የመሳሰሉትን ሲሆን የሥጋ ባሕርያት የሚባሉት ደግሞ መሬትነት፣ እሳትነት፣ ውኃነትና ነፋስነት ናቸው፡፡ በጌታችን ተዋሕዶ እነዚህ ሁለት ባህርያት በተፀቅቦ /በመጠባበቅ/ አንድ ሆነዋል፡፡ ይህንንም ጌታችን ያደረጋቸው አንዳንድ ተዓምራት በግልፅ ያስረዳሉ፡፡ ለምሣሌ ያህል የተወሰኑትን እንመልከት፡፡

ጌታችን በመንገድ ሲያልፍ ከመወለዱ ጀምሮ እውር የነበረ ሰው አየና ወደ መሬት እንትፍ ብሎ በምራቁ ጭቃ አድርጎ በጭቃው የእውሩን ዓይኖች ቀባና ሂድ በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፡፡ እያየም ተመለሰ ዮሐ. 9፥1-10 በዚህ ታሪክ ውስጥ የዓይነ ሥውሩን ዐይን ያበራው ማነው? ሥጋ ነው? እንዳንል፡፡ ለሥጋ ይህንን ማድረግ በራሱ አይችልም፡፡ መለኮት ነው? ብቻ እንዳንል ለመለኮት ምራቅ የለውም፡፡ ነገር ግን ሥጋን የተዋሀደ መለኮት በለበሰው ሥጋ /እንደሰውነቱ/ ምራቁን ወደ መሬት እንትፍ አለና እንደ አምላክነቱ ደግሞ ዓይኑን አበራው፡፡

ሐዋርያት በታንኳ ተሳፍረው በሚጓዙበት ጊዜ ጌታችን በባህር ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ ይመጣ ነበር ሐዋርያትም ምትሐት መስሏቸው ፈሩ ነገር ግን ጌታችን እርሱ እንደሆነ ነገራቸው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም በውሃው ላይ እንዲሄድ ጌታን ለመነው ጌታችንም ፈቀደለት እርሱም በባህር እየተራመደ ወደ ጌታ መጣ፡፡ ነገር ግን የነፋሱን ኃይል ዓይቶ ስለፈራ ይሰጥም ጀመረ፡፡ ወዲያውም ጌታ ሆይ አድነኝ ብሎ ጮኸ ጌታችንም እጁን ዘርግቶ ያዘውና ገሰፀው ወደ ታንኳይቱም አብረው ገቡ፡፡ ማቴ .14፥24-33

በዚህ ታሪክ ውስጥ በባህር ላይ የተራመደው ማነው? ሥጋ ነው እንዳንል ሥጋ በራሱ እንደዚህ ዓይነት አቅም የለውም:: መለኮት ብቻ ነው እንዳንል መለኮት አይዳሰስም የገዘፈ የሚታይ አካልም የለውም ነገር ግን ቃል በተዋሐደው ሥጋ ይህን አደረገ እንላለን:: የመለኮት ገንዘብ የሥጋ ገንዘብ፣ የሥጋ ገንዘብ የመለኮት ገንዘብ ሆኗልና እንላለን::

በገሊላ ቃና ሠርግ በሆነ ጊዜ ጌታችን ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተገኘ:: ሠርገኞቹ የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ በእመቤታችን አማላጅነት ስድስቱ የድንጋይ ጋኖች የተሞሉት ውሃ ወደ ወይን ጠጅነት ተለወጠ:: ዮሐ. 2፥7-10 ይህንንስ ያደረገው ማነው? ሥጋ ነው? እንዳንል ሥጋ በራሱ ድንቅ ተአምራትን አያደርግም፣ መለኮት ነው? እንዳንል መለኮት ይበላና ይጠጣ ዘንድ በሰርግ ቤት አይገኝም በግዝፈት ይገለጥ ዘንድ ባህርይው አይደለምና:: ነገር ግን ውሃውን የለወጠው ሥጋን የተዋሀደ መለኮታዊ ቃል ነው::

እነዚህና የመሣሠሉት ተዓምራት መለኮት ከሥጋ ጋር ፍፁም መዋሀዱን ይናገራሉ:: ከእነዚህም በተጨማሪ ራሱ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱም የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትም ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ከሁለት አካል አንድ አካል መሆኑን በሥፋት ያስረዳሉ:: ይህንን በሌላ ርዕስ የምንመለከተው ይሆናል:: አሁን ግን አባቶች የመሰሉልንን የተዋሕዶ ምሣሌዎች እንመልከት::

### *2.3 የተዋሕዶ ምሳሌዎች*

ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ለጢሞቴዎስ እንደነገረው «እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው::» 1ጢሞ. 3፥16 ነገር ግን ለኛ በሚገባን መልኩ አባቶቻችን አንዳንድ ምሣሌዎችን ነግረውናል:: ነገር ግን ይህንን ድንቅ ምሥጢር ሊገልፅ የሚችል ፍፁም ምሳሌ የለም::

24ኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስ የተዋሕዶን ምስጢር በብረትና በእሳት መስሎታል:: ብረት እሣት ውስጥ ቢገባ እንደ እሣት ቀይ ይሆናል:: እሣቱም የብረተን ቅርፅ ይይዛል:: ከዚህ በኋላ እሣት ወይም ብረት አይባልም የጋለ ብረት ይባላል እንጂ:: ብረቱ እሣቱ ውስጥ ከመግባቱ በፊት መመታት ይችላል ግን አይለዝብም እሣት ውስጥ

ከገባ በኋላ ግን ይለዝባል። የጋለ ብረትን በመዶሻ ብንመታው፣ የመታነው ማንን ነው? እሣቱን ነው እንዳንል እሣት አይመታም ረቂቅ ነው። ብረቱን ብቻ ነው እንዳንል ብረት ብቻውን አይለዝብም። ነገር ግን እሣቱ የብረቱን ቅርፅ ይዞ ብረቱም የእሳቱን ገንዘብ ገንዘቡ አድርጎ ይመታል። የሥጋና የመለኮት ተዋሕዶም እንደ ብረትና እንደ እሣት ተዋሕዶ ነው የሥጋ ገንዘብ ለቃል፣ የቃል ገንዘብ ለሥጋ በተዋዶ ሆኗልና።

431 ዓ.ም የተደረገውን የኤፌሶን ጉባኤ በሊቀ መንበርነት የመራው አባታችን ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ለመናፍቁ ለንስጥሮስ የተዋሕዶን ትምህርት በነፍስና በሥጋ ተዋሕዶ መስሎ ነግሮታል። አንድ ሰው የነፍስና የሥጋ ውህድ ነው። ነገር ግን ሁለት ሰው አይባልም። ለምሣሌ አንድ ጸሐፊ ከጻፈ በኋላ የጻፈው ሥጋው ወይስ ነፍሱ መሆኑን ብንጠይቀው ግራ ሊጋባ ይችላል ምክንያቱም የሚጽፈው ነፍሱን የተዋሀደው ሥጋው ነው። የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶም የነፍስና የሥጋ ተዋሕዶን ይመሰላል። የነፍስ ሥራ ይኼ ነው፣ የሥጋም ሥራ ይኼ ነው ተብሎ እንደማይከፈል ሁሉ ከተዋሕዶ በኋላ የሥጋ ሥራ፣ የመለኮት ሥራ ተብሎ ከሁለት አይከፈልም መለኮትን የተዋሐደ ሥጋ /ሥግው ቃል/ ሠራ ይባላል እንጂ።

ሆኖም ግን እነዚህ ምሣሌዎች ተዋሕዶን ፈፅሞ የሚገልፁ አይደሉም ሕፀፅ አለባቸው። የተዋሕዶ ምስጢ ር ሊፃፍም ሊነገርም ከሚችለው በላይ ረቂቅ ነውና። ምስጢርን የሚገልጽ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር የረቀቀውንና የራቀውን ምስጢር ይግለፅልን። አሜን።

### *2.4 የተዋሕዶ አስፈላጊነት*

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ሰው ሳይሆን አዳምን ማዳን ሲችል ለምን ሰው እንደሆነ ይጠይቃሉ። እግዚአብሔር አምላክ ከሀሌ ኩሉ እንደመሆኑ መጠን ሰው ሳይሆን አዳምን ማዳን ቢችልም የመለኮት ከሥጋ ጋር መዋሐድ ግን አስፈላጊ ነበር።

ከላይ እንደተመለከትነው አዳም የበደለውን በደል የመካስ አቅም አልነበረውም ነገር ግን እንዲድን ከተፈለገ የግድ መለኮት የአዳምን ሥጋ ተዋሕዶ መገለጥ ነበረበት። ከዚህም በተጨማሪ አዳም ሞት ነግሶበት ለ5500 ዘመን ኖሯልና ጌታችን ሥጋን ተዋሕዶ አድኖታል። በሌላም በኩል ዲያብሎስ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ አዳምን ከእግዚአብሔር ቢለየው ጌታችን ሥጋን ተዋሕዶ አድኖታል። በተረቱበት መርታት ልማድ ነውና።

### *2.5 በተዋሕዶ ላይ የሚነሱ የተሳሳቱ አመለካከቶች*

ጌታችን ሰው የሆነው በተዋሕዶ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ከእዚህ ውጪ ግን በጌታችን ተዋሕዶ ላይ የሚነሱ የተሳሳቱ አመለካከቶች አሉ፡፡ እንደሚከለተው እንመለከታቸዋለን፡፡

1. **እንበለ ውላጤ /ያለመለወጥ/**

አንዳንዶች የጌታችን ሰው መሆን በመለወጥ መሆኑን ያስተምራሉ፡፡ ይህም የቃና ውሃ ወደ ወይን እንደተለወጠ፤ የሎጥ ሚስትም ወደ ጨው ሐውልትነት እንደለወጠች መለኮትም ከመለኮትነት ወደ ሥጋነት ተለውጧል የሚሉ አሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ትምህርት ከነገረ ድህነት አንፃር ስንመለከተው እጅግ ከንቱ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሰው ሰውን ሊያድነው አይችልም፡፡ መለኮት ሰው ወደ መሆን ተለውጣል ካልን ፍፁም ሰው ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በቀጥታ ከነገረ ድህነት ትምህርት ጋር ይጋጫል፡፡ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ የሚያድን የለም» ኢሣ. 43፥11፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውላጤን ትምህርት ማመን ክርስቶስ በከንቱ እንደሞተ ማመን ነው፡፡ ምክንያቱም አዳምን ሰው ማዳን ቢችል ኖሮ ከአቤል ጀምሮ እስከ ዘካርያስ ድረስ የፈሰሰው የነቢያት ደም ባዳነው ነበር፡፡ ራሱም እግዚአብሔር በቃሉ «እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፡፡» ሲል ተናግሯል፡፡ ሚል. 3፥6 ቅዱስ ጳውሎስም በመልዕክቱ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና ዛሬ እስከዘላለም ያው ነው» ሲል ገልጿል፡፡ ዕብ. 13፥8 በተለይ በዚህ ዐረፍተ ነገር ትላንትና ብሎ ቅድመ ሥጋዌውን፤ ዛሬ ብሎ መዋዕለ ሥጋዌውን እስከ ዘላለም ብሎ ድህረ ሥጋዌውን ገልፆ በሦስቱም ጊዜያት እንዳልተለወጠ እደማይለወጥም አመልክቷል፡፡ ቅዱስ ኤፍሬምም በድርሰቱ «ዘኮነ ሰብአ ዘእንበለ ፍለጠት ወኢውላጤ መለኮት ንጹህ ዘአልቦ ሙስና» ያለመለየትና ያመለወጥ ሰው የሆነ ይኸውም መለወጥ የሌለበት ንፁህ መለኮት ነው፡፡» ብሎአል፡፡ ወ.ማ.ዘሰንበት

2. **እንበለ ሚጠት /ያለመመለስ/**

የሥጋና የመለኮት ተዋሕዶ ወደ አለመዋሐድ የሚመለስ አይደለም፡፡ ሚጠት ማለት መመለስ ማለት ሲሆን ማየ ግብፅ /የግብጽ ውኃ/ አስቀድሞ ውሃ በመቀጠልም ደግሞ ደም ከዚያም ተመልሶ ውሃ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ በትረ ሙሴ አስቀድሞ በትር

በኋላም እባብ በመቀጠልም ተመልሳ በትር እንደሆነች መለኮትም አስቀድሞ መለኮት ከዚያም ሥጋ በኋላም ተመልሶ መለኮት እንደሆነ የሚናገሩ አሉ። የሚጠት ትምህርት ብዙም ከውሳጤ ያልተለየ በመሆኑ ከላይ የተናገርናቸው ነገሮች በሙሉ ለእነዚህም ይሠራሉ። ከዚህም በተጨማሪ መለኮት ከህሊ ኩሉ እንደመሆኑ መጠን ሥጋ መሆን ቢችልም ሥጋ ግን ወደ መለኮትነት የመመለስ ስልጣን የለውም ይህም የሚጠት ትምህርት እርስ በራሱ የሚጣላ መሆኑን ያመለክታል። እኛ ግን ጌታችን በተዋሕዶ ሰው እንደሆነ እናምናለን።

## 3. እንበለ ህድረት

የህድረት ትምህርትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማረው የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ መናፍቁ ንስጥሮስ ነው። ንስጥሮስ «እመቤታችን የወለደችው አምላነክነት የሌለው ሰው ብቻ ነው» ይላል። «ኋላ ግን ሲጠመቅ የአብ ልጅ መጥቶ አደረበት በዚህም የጸጋ አምላክነትን አገኘ» በማለት የህድረትን ምንፍቅና አስተማረ። ህድረት ማለት ሰይፍ በሰገባው፣ ዳዊትም በማህደሩ እንደሚያድር እንዲሁ መለኮት በሥጋ እንዳደረበት የሚናገር ኑፋቄ ነው። ነገር ግን ጌታችን ከመጠመቁ በፊት አምላክ እንደሆነ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። «ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል. . . ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ. . .» ኢሳ. 9÷6። ቅዱስ ገብርኤልም «እርሱም ታላቅ የልዑል ልጅ ይባላል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም» በማለት ከጥምቀት በፊት አምላክ መሆኑን አብስሯል። ሉቃ. 1÷32። መጥመቁ ዮሐንስም በማኅጸን ሆኖ ለጌታ የአምልኮት ስግደት ለእመቤታችን የፀጋ ስግደት በመስገድ ጌታችን እንኳን ከመጠመቁ ከመወለዱ በፊት አምላክ መሆኑን በተግባር አሳይቷል። እናቱ ቅድስት ኤልሣቤጥም «የጌታዬ እናት» ሉቃ. 1÷43 /በማለት/ እመቤታችን ወላዲተ ሰብእ ሳትሆን ወላዲተ እግዚእ፣ ወላዲተ አምላክ እደሆነች ተናግራለች። ሰብአ ሰገልም ከምስራቅ በመምጣት ለተወለደው ሕፃን ሰግደዋል።

## 4. እንበለ ቱሳሔ /ያለመቀላቀል/

ቱሳሔ ማለት መቀላቀል ማለት ነው። እንደ ማርና እንደ ውሃ፣ እንደ ቡናና እንደ ወተት ማለት ነው። ማርና ውሃ ሲቀላቀሉ ውሃው ማሩን አሟምቶ ማሩም ውሃውን ያጣፍጠዋል። እንዲሁ ደግሞ ቡናና ወተት ሲቀላቀሉ ቡና ወተቱን አጥቁሮ ወተቱም ቡናውን ያነጣዋል ጣዕም ማዕከላዊ መልክዕ ማዕከላዊ ይሆናል። በቱሳሔ ትምህርት

መለኮት ከሥጋ ጋር ተቀላቅሏል። ማርና ውሃ ሲቀላቀሉ ሁለቱም ባህርያቸውን ለቀው መካከኛ ብርዝ እንደሚገኝ እንዲሁ ደግሞ ቡናና ወተት ሲቀላቀሉ ሁለቱም ባህርያቸውን ለቀው መካከለኛ ማኪያቶ እንደሚሆኑ በቱሳሔ ትምህርት መለኮትና ሥጋ ባህሪያቸውን ለቀው መካከለኛ ነገር ተፈጥሯል የሚሉ ናቸው።

ይህ ግን ከብዙ ነገሮች አንጻር ስህተት ነው። የመጀመሪያው ከመዳን ትምህርት አንፃር ሲሆን ሰውን ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ እንጂ መካከለኛ ነገር አይደለም። በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል ያለ ፍጡር አዳምን ማዳን ቢችል ኖሮ ነቢያት ይልቁንም ደግሞ መላእክት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆነው አዳምን ባዳኑት ነበር። ከዚህም ውጪ መለኮት ለቅዕበት ያህል እንኳ ባህርይውን አለቀቀም ሥጋም እንዲሁ ቱሳሔ ካልን ግን እግዚአብሔርን ከእግዚአብሔርነቱ እንደማዋረድ ነው። በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ግን ጌታችን ሰው የሆነው እንበለ ተሳሔ /ያለመቀላቀል/ በተዋሕዶ ነው።

## 5. እንበለ ቡዐዴ /ያለመወዳጀት/

ቡዐዴ ማለት መወዳጀት /የወዳጅነት/ ማለት ነው። እንደ ዛቢያና እንደ ምሣር። ዛቢያና ምሣር ሲያስፈልግ እንደሚገናኙ አለበለዚያም እንደሚለያዩ በቡዐዴ ትምህርት መሠረት «ለመለኮትና ለሥጋም እንደዚሁ ነው» የሚሉ አሉ። ሌላው «በቡዐዴ ትምህርት መከራን የተቀበለው ሥጋ ብቻውን ነው፣ ምክንያቱም ለመለኮት መታመም አይስማማውምና ይላሉ። ይህም በቀጥታ ከድህነት ጋር ስለሚያጋጭ ጌታችን ሰው የሆነው እንበለ ቡዐዴ /ያለመወዳጀት/ ለዘለዓለም እንደሆነ እናምናለን።

## 6. እንበለ ትድምርት /ያለመደረብ/

ትድምርት ማለት መደመር መደረብ ማለት ነው። ለትድምርት ትምህርት መሠረት ሰው ልብስ እደሚደርብ እንዲሁ በሥጋ ላይ መለኮት ተደርቧል የሚል ነው። በመሰረቱ ለመለኮት በሥጋ ላይ መደረብ አይችልም። ምክንያቱም ሥጋ እጅግ ደካማ ሲሆን መለኮት ግን ኃያል ነው። ከዚህም ውጪ መለኮት በሥጋ ላይ የመደረብ ባህርይ የለውም። ይህም ጌታችን ሰው የሆነው እንበለ ትድምርት መሆኑን ያሣያል።

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት እግዚአብሔር ሰው የሆነው እንበለ ውላጤ፣ እንበለ ሚጠት፣ እንበለ ህድረት፣ እንበለ ቱሣሔ፣ እንበለ ቡዐዴ፣ እንበለ ትድምርት በተዋሕዶ፣ በተአቅቦ /በመጠባበቅ/ ያመጠፋፋት ነው፡፡

## 3. **አንድ ባህርይ /One incarnate Nature/**

የምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት /Oriental Orthodox Churches/ የሚባሉት የኢትዮጵያ፣ የግብፅ፣ የህንድ፣ የአርመን፣ የሶርያ አብያተ ክርስቲያናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋህዶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ መሆኑን ያምናሉ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት የተከፈለችበት ዋናው ምክንያት የአንድ ባህርይ እና የሁለት ባህርይ ትምህርት ነው፡፡

ባሕርይ ሳንል የመለኮትና የሥጋ ባሕርይን ማለታችን ነው፡፡ የመለኮት ባሕርይ ምሉዕ፣ ረቂቅ፣ ኃያል፣ ባዕድ፣ ሕያው ወዘተ ሲሆን የሥጋ ባሕርይ ደግሞ ውሱን፣ ግዙፍ፣ ድኩም ነዳይ፣ መዋቲ ወዘተ ነው፡፡

በ451 ዓ.ም በተደረገው የኬልቄዶን ጉባኤ በሮማው ፖኘ ሊዮን ሁለት ባሕርይ በሚል ደብዳቤ የተመሩት የቁስጥንጥንያና የሮም አብያተ ክርስቲያናት የሁለት ባህርይ የሚል አዲስ አሳብ በማምጣት ኑፋቄ ሲያቀርቡ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ዲዮስቆሮስና ተከታዮቹ በተዋህዶ አንድ ባህርይ ብለው ጉባኤውን ጥለው ወጥተዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ይህንን ጉባኤ፤ ጉባኤ ከለባት /የውሾች ጉባኤ/ በማለት ይጠሩታል፡፡

ኦርቶዶክሳዊያን ክርስቲያኖች በአንድ ባህርይ የሚያምኑት ከሁለቱ ባሕርያት የአንዱን የክርስቶስ ባህርይ ክደው አይደለም፤ በሁለቱ ባህርያት የባሕርየ የመለኮትና የባሕርየ ሥጋን ተዋህዶ በማመን እንጂ፡፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን የሰውነት ባህርይም ሆነ የአምላክነት ባህርይ አትክድም፡፡ ነገር ግን ጌታችን በተዋህዶ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ እንደሆነ ታምናለች፡፡

የጌታችንን የባህርይ ተዋህዶ መላእክት፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ እግዚአብሔር አብ፣ ሐዋርያት እንዲሁም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መስክረዋል፡፡ ይህንንም አንድ በአንድ እንመለከተዋለን፡፡

## 1. የመላእክት ምስክርነት

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እመቤታችን ለብስራት በተላከበት ወቅት ስለምትፀንሰውና ስለምትወልደው ልጅ «በያቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል፤ ለመንግስቱም መጨረሻ ያለውም» ብሎአታል:: ሉቃ. 1፥33:: /መፀነስና መወለድ የሰው ባህርይ ሲሆን ፍፃሜ የሌለው የመንግስት ባለቤትነት ደግሞ የአምላክነት ባህርይ ነው/:: የቅዱስ ገብርኤል ብስራት ሁለቱ ባህርያት እንደተዋሀዱ ያመለክታል:: ዳግመኛም የጌታን ልደት ለእረኞቹ ያበሰረው መልአክ «አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል» ብሏቸዋል:: ሉቃ. 2፥10 ይህም በዳዊት ከተማ በሥጋ የተወለደው የማርያም ልጅ የመለኮትን ባህርይ እንደተዋሀደ ያመለክታል:: ቅዱስ ያሬድም ስለመላእክት በተናገረበት ድርሰቱ «ወሶበ ርእዩ እግዚኦሙ ዘአስተጋብአ ኩሎ ፍጥረታተ እንዘ ይነብር ውስተ ጎፅንኪ ወዘይሴሲ ለኩሉ ፍጥረት ይጠቡ ሐሊበኪ ከመ ሕፃን ኀሠሥዎ ውስተ አርያም ወበህየ ረከብዎ ምስለ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ ከመ ትካት» «ፍጥረትን ሁሉ የሚመግብ ጌታ በብብትሽ ተቀምጦ ጡትሽን እንደ ሕፃን ሲጠባ ባዩ ጊዜ በአርያም ፈለጉና በዚያም እንደ ቀድሞው ከአባቱና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አገኙት» አንቀጸ ብርሃን/ በማለት በቤተልሄም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ባህርይ እንደሆነ መላእክት መስክረዋል::

## 2. የቅዱስ ዮሐንስ /መጥምቁ/ ምስክርነት

ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ መጣ የተባለለት ቅዱስ ዮሐንስ በስብከቶቹ ሁሉ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ባህርይነት መስክሯል:: ይህንንም ለአይሁድ ሲናገር «እኔም አይቼአለሁ እርሱም የእግዘብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ» ብሏል:: ዮሐ. 1፥34:: ይሄም በዮርዳኖስ የተጠመቀው የእግዚአብሔር አብ የባህርይ ልጅ የሥጋን ባህርይ የተዋሀደው መሆኑን ልብ ይሏል:: ዳግመኛም ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችንን ከማጥመቁ አስቀድሞ «...እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተ ወደ እኔ ትመጣለህን?» ብሎ የራሱን ታናሽነትና፣

የክርስቶስን አምላክነት ይልቁንም ሥጋን የተዋሀደ መለኰትን ማጥመቅ እንደማይችል በትህትና ተናገሯል፡፡ አባቶቻችንም መለኰትን የተዋሀደ ሥጋን ያጠመቀው ቅዱስ ዮሐንስን መጥምቀ መለኰት የሚል ቅጽል ስም ሰጥተውታል፡፡

### 3. የእግዚአብሔር አብ ምስክርነት

እግዚአብሔር አብ ስለ ልጁ የባህርይ ተዋህዶ ሲመሰክር «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎአል፡፡ ማቴ. 3፥17 ይህም በዮርዳኖስ የተጠመቀው የማርያም ልጅ የአብ ልጅ መሆኑን ተናግሯል፡፡ ዳግመኛም በደብረ ታቦር ተራራ ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን በገለፀ ጊዜ «የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት» ብሎአል ማቴ. 17፥5፡፡ «ወልደ አብ ወልደማርያም» እንደሆነ የመሰከረው ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው፡፡ በዚህም ምስክርነቱ የአዳም ልጅ የሆነው ወልደ ማርያም በተዋህዶ ስለከበረ ወልደአብ እንደተባለ ያሥረዳል፡፡

### 4. የሐዋርያት ምስክርነት

ጌታችን ከዋለበት የዋሉት ካደረበት ያደሩት ሐዋርያት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባህርይ እንደሆነ በስፋት መስክረዋል፡፡ የሥጋዌን ምሥጢር በምልዐት የፃፈው ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ «ስለ ሕይወት.... የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ ሕይወት ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን» ብሏል 1ኛ ዮሐ. 1፥1፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ያየው፣ የተመለከተው የዳሰሰው፣ የማርያምን ልጅ ቢሆንም የመለኮትን ባህርይ ስለተዋህዶ «የህይወት ቃል» በማለት ጠርቶታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም «ጠላቶቹ ሳለን እግዚአብሔር በልጁ ሞት አዳነን» ብሏል፡፡ ሮሜ. 5፥10፡፡ ይህም በቀራንዮ ደሙን ያፈሰሰው የሥጋን ባህርይ ባህርይው ያደረገው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በወንጌልም ጌታችን አይነኑ ያበራለት ሰው በእግዚአብሔር ልጅ እንደሚያምን ሲጠይቀው ማን እንደሆነ መልሶ ጠይቆታል፡፡ ጌታችንም አይተኸዋል ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው፡፡ ዮሐ. 9፥37 ለዚህ ሰው የታየውና ዓይኑን ያበራለት በተዋህዶ የእግዚአብሔር ልጅ

መሆኑን ጌታችን ራሱ ነግሮታል፡፡ ዳግመኛም የጌታን የፍርድ ሂደት የጻፈው ቅዱስ ማርቆስ በወንጌሉ «የቡሩክ ልጅ ክርቶስ አንተ ነህን? አለው፡፡ ኢየሱስም እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ» በማለት ጽፏል፡፡ ማር. 14፥62፡፡ ይህም ጌታችን የተዋሀደው ሥጋ የመለኮት ባህርይ ገንዘብ የሆነውን የእግዚአብሔር ልጅነት በተዋሕዶ የባህርይ ገንዘቡ እንዳደረገ ያመለክታል፡፡

## 5. የሊቃውንት ምስክርነት

አባቶቻችን ሊቀውንተ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን የባህርይ ተዋህዶ በስፋትና በምልዐት አስተምረዋል፡፡ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም «ሎቱ ንስግድ ወንሰብሀ አሐዱ ህላዌ፡፡» እንስገድለትና እናመስግነው ዘንድ አንድ ባህርይ ነው፡፡» በማለት የባህርይውን ተዋህዶ ተናግሯል፡፡ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አትናቴዎስም፡፡ /«ወአስ ዘንብል በእንተ ዝንቱ ለወልድ ዋህድ በቱ ፪ቱ ህላዌያት ለ፩ዱ ዘንሰግድ ወለካልኡ ዘኢንሰግድ አላ ፩ዱ ህላዌሁ ለእግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ ወንሰግድ ሎቱ ምስለ ሥጋሁ አሐተ ስግደተ፡፡»..... ለወልድ ዋህድ ለአንዱ የምንሰግድለት ለአንዱ የማንሰግድለት ሁለት አካል ሁለት ባህርይ አለው የምንል አይደለንም፡፡ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር አካሉ ባህርዩ አንድ ነው አንጂ ከሥጋው ሳንለይ አንድ አድርገን አንዲት ስግደት እንሰግድለታለን እንጂ ይላል፡፡ ሃይማኖተ አበው ዘአትናቴዎስ፡፡ ሌላው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስም «ለገበ ንቤ በእንተ አማኑኤል ከመ ውእቱ እምህላዌ መለኮት ትስብእት ከመዝ ውእቱ እስመ ትስበዕት ናሁ ኮነ ለቃል ወ፩ዱ ወልድ ውእቱ ምስሌሁ፡፡ ከመለኮት ባህርይና ከትስብእት ባህርይ እንደተገኘ የአማኑኤልን ነገር ብንናገር እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋህዶ ነው፡፡ እነሆ ሥጋ የቃል ገንዘብ ሆኗልና፡፡ ከእርሱም ጋር አንድ ወልድ ነውና በማለት ተዋህዶውን መስክሯል፡፡ ሃ.አበው ዘቄርሎስ፡፡ ዳግመኛም ይኸው አባት ሁለት ባህርይ የሚሉ ንስጥሮሳውያንና ሊዮናውያንን ባወገዘበት ቃል እንዲህ ብሏል፡፡

«እመቦ ዘይቤ ቅድስት ድንግል ማርያም ኢወለዲቶ ለእግዚአብሔር ቃል በሥጋ ዘወለደቶ ውፁእ ውእቱ እመለኮት ውጉዝ ለይኩን፡፡ ቅድስት ድንግል

ማርያም የእግዚአብሔር ቃልን አልወለደችውም የወለደችውም አምላክነት የሌለው ነው የሚል ቢኖር የተወገዘ ይኹን» ብሏል፡፡ ቃለግዝት ዘቄርሎስ፡፡

መላእክት፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ እግዚአብሔር አብ፣ ሐዋርያትና ሊቃውንት እንደመሰከሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባህርይ ነው፡፡ እኛም አባቶቻችን ሐዋርያት እንዳስተማሩን የአካልና የባህርይን ተዋህዶ እናምናለን፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤራቅሊስ እንደተናገረው የተዋህዶ ምሥጢር በሰው ሁሉ ልብ ከመመርመር የራቀ ነውና የተዋህዶን ምሥጢር ከመጠን አልፈን አንመራመር፡፡ ይልቁንም ምሥጢሩን የሚገልፅ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ይግለፅልን፡፡ አሜን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር